
# ከሸአቢያ መልካም ነገርን ከኵርንችት የወይን ፍሬን ማግኘት ይቻል ይሆን?

**ከጎልጉል ድረገጽ ጋዜጣ የተወሰደ**

(ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው)



January 7, 2015 8:14

ኢትዮጵያ ሆይ! አሁንስ ተስፋሽ ማን ነው እግዚአብሔር አይደለምን?

መቸስ በጣም ይገርማል! ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ መከራችን ሊያልቅ ነው ስንል ገና መጀመሩ ነው እንዴ ጃል? ጉድ እኮ ነው! የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ለመሆኑ ከዚህ በላይ ሌላ የመከራ ዘመናት መሸከም የሚችል ትከሻ አለህን?

የአርበኞች ግንባር ግንቦት 7 ሌሎችም በትጥቅ ትግል ላይ ያሉ ኃይሎች ውሕደት ሊፈጽሙ እንደሆነ ካስታወቁ ወራት ተቆጥረዋል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ደርሶ በይፋ ለሕዝብ ከማስታወቃቸው በፊትም ከዚህ መግባባት ላይ ለመድረስ አጭር የማይባል ጊዜ እንደወሰደ መገመት ይቻላል፡፡ ይሄም ሆኖ "ታጋይ ኃይሎቹ ሊዋሐዱ እንደሆነ ካስታወቁ በኋላ ግን ዓላማቸው ያን ያህል ግልጽና ተጣጣሚ የሚፈልጉትም ከሆነ ምን አንጓተተው?" የሚለው ጥያቄ ከብዙዎች የሚነሣ ጥያቄ ነበረ፡፡ አሁን ግን የዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ግልጽ እየሆነ መጥቶ የሸአቢያ ሸረኛ እጅ መሆኑ ታውቋል፡፡

ቀድሞም ቢሆን ወያኔ አጎራባች ሀገሮችን በሙሉ የሀገራችንንና የሕዝቧን ብሔራዊ ጥቅሞች አሳልፎ እየሰጠ በጥቅም ስለያዛቸውና እሱ በትግል ላይ እያለ ከሱዳን ያገኝ የነበረውን ሁለንተናዊ ድጋፍ ዓይነት እንኳን ባይሆን ተገን ብቻ እንኳን ከአጎራባች ሀገሮች ማግኘት የሚቻልበትን ዕድል ሙሉ ለሙሉ ዝግ ስላደረገው ቢጨንቃቸውና አማራጭ ቢያጡ በሀገራችን በሰላማዊ ትግል መንግሥታትን መቀያየር የሚቻልበት የትግል አማራጭ ሙሉ ለሙሉ ዝግ በመሆኑ የቀረልን የተተወልን አማራጭ የትጥቅ ትግል ከሆነ ያለን ብቸኛ አማራጭ ሰሜናዊው የሀገራችን ክፍል ባሕረ ምድር (ጣሊያኖች ኤርትራ ብለው የሠየሟት ይሄንን ተቀብለን እኛም መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎቹም ሳይቀር ኤርትራ እያልን የምንጠራት) ብቸኛዋ አማራጭ በመሆኗ እንጅ የሸአቢያን ማንነት ዘንግተው ሸአቢያን ከማመን አንጻር እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ይመስለኛል፡፡ ዋናው የመርዙ ሰንኮፍ ማን ሆነና? ይሄንን እንዴት እንረሳለን?

እኔ በግሌ ለአርበኞች ግንባርና ለግንቦት 7 ድጋፌን የምሰጠው እጅና እግርን አጣጥፎ ግፍን እየተጋቱ የሌለ ነገርን ተስፋ እያደረጉ አርፎ ተቀምጦ ከመረገጥ ችግር እንዳለ ቢታወቅም የተገኘውን አማራጭ ሁሉ መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ ነበር እንጅ እነዚህን ወገኖቻችንን ሀገራችንን እንደሚመቻት እንደሚበጇትና እነሱም እንደሚመኙት ሳይሆን ሸአቢያ ለራሱ እንደሚመቸውና እንደሚበጀው ለማድረግ ጣልቃ እንደሚገባባቸውና በርካታ መሰናክሎችን እንደሚጋርጥባቸው ጠፍቶኝ አልነበረም፡፡

ለዚህች ሀገር ጠላት ካልን ከወያኔም ሻአቢያ እንደሚከፋ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ሻአቢያ ለራሱ ጥቅም ሲል ወያኔ እንዲጠፋለት የሌት ተቀን ምኞቱና ሕልሙ ስለሆነ እራሱም እንዳያደርገው አቅም ስለሌለው ለወያኔ አቅም የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሱን ጥቅም ለማስጠበቅ የተነሡ ልጆቹን በመያዝ በሚያደርጉት ትግል ወያኔን ለመጣል በማሰብ "የጠላቴ ጠላት ወዳጀ" በሚል ስሌት ተቀበላቸው እንጅ ለኢትዮጵያ መልካምና ቀና ከማሰብ ከመመኘት እንዳልሆነ አሁንም በጣም ግልጽ ነው፡፡

እነዚህ ወገኖቻችን በተግባር ምን እንዳጋጠማቸው ባላውቅም የሀገርን ጥቅም አሳልፈው ለመስጠት እንዳይገደዱ፣ የሻአቢያንም አላስፈላጊ የስምምነት ጫና ለመቋቋም ማድረግ ያለባቸውን ጥንቃቄ ያደረጉ ይመስለኛል፡፡ ዓላማቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በኃይል የተጫነውን አንባገነንና የጥፋት ኃይል ወያኔን ከሥልጣን እስከማስወገድና የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት እስከማድረግ ድረስ ብቻ እንጅ በወያኔ ተተክተው በሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመፈናጠጥ እንዳልሆነ ግልጽ አድርገዋል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያና በሕዝቧ ጥቅሞችና ሀብት ላይ ከማንም ጋራ የመደራደር ኃላፊነትና መብት ስለሌላቸው ይሄንን ማድረግ እንደማይችሉ ለሁሉም አረጋግጠዋል፡፡ ሻአቢያ ይህ የወገኖቻችን አቋም እነሱን በመጠቀም ጥቅሙንና ፍላጎቱን ለማስጠበቅ እንዳይችል አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ይሄንን ፍላጎቱን የሚያሟላ ሌላ አማራጭ በማፈላለግና በመፍጠር ተግባር ተጠምዶ ቆይቶ ጥረቱ ያዘለትና ደሚሕትን ወይም ትሕዴንን መፍጠር ቻለ፡፡ በአጭር ጊዜም የአርበኞች ግንባርንና ግንቦት ሰባትን ብለው ወደ ባሕረ ምድር (ኤርትራ) የሚገቡትን ዜጎችን ሁሉ ወደ ደሚሕት ማለትም ትሕዴን (የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) በማስገባት ትሕዴንን ከፍተኛ የተዋጊ ቁጥር እንዲኖረውና እንዲጠናከር በማድረግ የሩቅ ትልሙን ለማሳካት ጥሩ መሠረት ፈጠረ፡፡

ሻአቢያ ትሕዴንን እንዲህ ካደረገ በኋላ ለግንቦት ሰባትና ለአርበኞች ግንባር ያለው ስሜት እየተቀዛቀዘ መጥቷል አሁን እነሱን ሊጠቀምባቸው የሚፈልገው ለመቆመሪያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለያ ለመደለያነት ያህል ነው፡፡ ይሄንንም እነኝሁ ወገኖቻችን ጠንቅቀው ያውቁታል ብየ እገምታለሁ፡፡ ሻአቢያ ኢትዮጵያን የሚል ለሀገሩ ታማኝ የሆነ ኃይል ለእሱ እንደማይበጀው ያስባልና በእርግጥም ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ታማኝ ለሆነ ኃይል ምን ዓይነት አመለካከት አስተሳሰብ ሊኖረው እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ እኛን ሀገርን ብለው ትግል የወጡ ወገኖቻችን አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ስለ መፍትሔው እያንዳንዱ ዜጋ ጠልቆ ማሰብ ይኖርበታል "በቃ! ተስፋ የላቸውምና እነሱን መተው መርዳትና መደገፍ ማቆም ነው መፍትሔው" ብሎ የሚል ደንቆሮ ዜጋ እንደማይኖር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በእኔ ግምት እነሱን መታደግና የወጡለትን ዓላማ ለስኬት ማብቃት የምንችለው በገፍ ወደ እነሱ በመግባት ያለውን የኃይል ሚዛን አለመመጣጠን መቀልበስ የቻልን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በተቻለ መጠንም ደሚሕትን መቀላቀል ሳይፈልግ ትግሬም ሳይሆኑ ወደ ደሚሕት እንዲቀላቀል የተደረገው አብዛኛውን የደሚሕትን ታጋይ ወደ ሚፈልገው አርበኞች ግንባር ወይም ግንቦት 7 እንዲቀላቀሉ ማድረግ የሚቻልባቸው መንገዶች መሞከር መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

በበርካታ ምክንያቶች ወያኔና ሻአቢያ ቀድሞ የነበራቸውን ቃልኪዳን ዝምድና ወዳጅነት አንድነትና ጥምረት ከምናውቀውም በላይ ነበር፡፡ ያ የወያኔ ቃል ኪዳንና ዝምድና እንኳን በእኛ በእነሱም እንኳ መቸም ይደፈርሳል ይፈርሳል ተብሎ ሳይጠበቅ ሳይታሰብ ተአምር ሊባል በሚችል ደረጃ የሆነውን ለማመን ሁሉም በተቸገረበት መልኩ ቃል ኪዳናቸው ፈረሰ የሆነው ሁሉ ሆነ፡፡ ያ ቃል ኪዳናቸው ዳግም ላይታደስ ፈረሰ፡፡ ይህ ማለት ግን ሻአቢያ ወያኔ ከወጣበት ኅብረተሰብ ሌላ ኃይል ቢወጣለት ደስታው አይደለም ቃልኪዳንም አይመሠርትም ማለት አልነበረም፡፡ ቅድሚያ የሚሰጠውና ተመራጭ የሚያደርገው ጉዳይ ይሄ እንደሆነ ማንም ሊያውቀው ይገባል፡፡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በተመለከተ ሻአቢያ ድሮም አሁንም ወደፊትም ያው ነው መቸም ይለወጣል ብየ አልገምትም፡፡

የደሚሕት ኃይል በዚህ መልኩ ተጠናክሮ ከመውጣቱ ጋራ በተያያዘ ሻአቢያ የልቡ ደርሷል የሐሳቡ ሰምሯል፡፡ ስለሆነም ሻአቢያ ሳይወድና ሳይፈቅድ ወያኔን ለማጥቃት ሲል ብቻ ኢትዮጵያን ከሚጠቅሙ ኢትዮጵያን ካሉ ኃይሎች ጋር ከአርበኞች ግንባርና ከግንቦት 7 ጋር አብሮና ተባብሮ ኢትዮጵያን ተጠቃሚ ማድረግ ግድ ሳይለው ኢትዮጵያን በተመለከተ ቀድሞ ከነበረው አቋሙ አንዲት ጋትም ብትሆን ፈቀቅ ማለት ሳያስፈልገው በብዙ ምክንያቶች ወገኑ ዘመዱ የቃልኪዳን አጋሩ አድርጎ ከሚቆጥረው ኅብረተሰብ የሚፈልገውን ኃይል አግኝቷልና ከላይ እንዳልኩት ለመደለያ ለመቆመሪያ ካልሆነ በስተቀር የግንቦት 7ን እና የአርበኞች ግንባርን ኃይሎች ትርጉም ያለው ፋይዳ አዘል ሚና ሊጫወቱ በሚችሉበት መልኩ ተጠናክረው መውጣታቸውን ፈጽሞ አይሻም፡፡ እያደረገ ያለው ጣልቃገብነትም ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው ይሄንን ሀቅ ነው፡፡

እኔ እንደ ደምሒት(ትሕፌን) እና አረና ትግራይ ዓይነት ብሔር ተኮር ለሆነ የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ የትጥቅ ትግል ኃይል በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ጥሩ አመለካከት የለኝም፡፡

1. ከወያኔ እንደተማርነው የብሔረሰብን ጉዳይ የፖለቲካው ጅማሬና ፍጻሜ ያደረገ የትኛውም ፓርቲም ሆነ የትግል ኃይል ሥልጣን ቢይዝ ጉዳዩ ዓላማው ተግባሩ ሁሉ ብሔሬ የሚለውን ብሔረሰብ ለመጥቀም ተጎድቷል ከሚለው ለመካስ እሱም በተራው በሌሎቹ ላይ ለመፈናጠጥ ለመፋነን ከመጣር የተለየ ሊያደርግ አይችልም፡፡ እጅግ አሳዛኝ በሆነ ደረጃ እንጭጮች ናቸው ጠባቦች ናቸው ያልበሰሉ ናቸው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሕዝብና ለሀገር ትርጉም ያለው ሥራ ሊሠሩ የሚችሉትና ፋይዳ የሚኖራቸው ሥልጣን በያዙ ጊዜም ፍትሕና እኩልነትን ለማስፈን የታመኑ የተጉ ሊሆኑ የሚችሉት ጠባብ ከሆነው የብሔር ተኮር አስተሳሰብ ወጥተው እንደ ሰው አስፍተው ማሰብ ሲችሉና እንደ ዜጋም ሀገር የምትባልን ሥዕል በጭንቅላታቸው ውስጥ ማስፈር ቦታም መስጠት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

አለዛ ግን ሥልጣን በያዙ ጊዜ እንደወያኔ ሁሉ የሌሎቹን ብሔረሰቦች መብቶችና ጥቅሞች እየረገጡ ተጎዳ ተበደለ ተጨቆነ ተጋደልንለት ሞትንለት መሥዋዕትነት ከፈልንለት የሚሉትን ብሔረሰባቸውን ብቻ ለመካስ ለመጥቀም ለማስደሰት ነው የሚጥሩት እንጂ ሁሉንም ዜጎች በእኩል ተመልክተው የፍትሕንና የእኩልነትን ጥያቄ የሚመልሱ የሚፈቱ አይሆኑም ተፈጥሯቸው አይፈቅድላቸውምና፡፡ ከዚህ ቁንጽል አስተሳሰብ መውጣት አስካልቻልን ጊዜ ድረስ የደም መፋሰስ በዚህች ሀገር ውስጥ ይቆማል ብላቹህ ተስፋ አታድርጉ፡፡ ትሕዴንና አረና ትግራይ ስማቸው እንደሚያመለክተው ሐሳባቸውና ዓላማቸው የትግራይን ሕዝብ ከወያኔ በተሻለ ተጠቃሚ ለማድረግ እንጅ እንደኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያን አስበው ኢትዮጵያ አቀፍ ዓላማና ሐሳብ አንግበው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ማዕከል በማድረግ አይደለም፡፡ እነዚህ አካላት በተደጋጋሚ ሲገልጹት እንደተሰማው ለመመሥረታቸው ምክንያታቸው “የትግራይ ሕዝብ በወያኔ ተከድቷል የተገባለት ቃል አልተፈጸመለትም” የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ዓላማቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከወያኔም የከፋ ወያኔ ለመሆን ነው ማለት ነው፡፡

2. ደሚሕቶች ከአርበኞች ግንባር ጋር አብሮ ለመሥራት በተነጋገሩ ጊዜ ሊያግባባቸው ያልቻለው ጉዳይ ኢፍትሐዊ በሆነና በግፍ በታጀበ መንገድ ከጎንደርና ከወሎ እየተቆረሰ ወደ ትግራይ የተከለለው መሬት ጉዳይ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ከልብ ይሁን አይሁን ባይታወቅም ደሚሕቶች በመርህ ደረጃ ከአርበኞች ግንባር አቋም እንዲይዙ የተጠየቁትን ቢስማሙበትም ለጊዜው ግን “የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ ያሳጣናል” በሚል ሰበብ “ከጎንደርና ከወሎ ተቆርሰው ወደ ትግራይ የተከለሉትንና እየተከለሉ ባሉ መሬቶች ላይ አቋም ወስደን ለሕዝብ ይፋ የምናደርገው ነገር ስለማይኖር ከድል በኋላ እልባት እንሰጠው አሁን ግን በትግሉ ላይ እናተኩር” የሚል የብልጥ አይሉት የሞኝ አቋም በመያዛቸው መግባባት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ደሚሕቶች የትግራይን ሕዝብ ማዕከል ባደረጉ በሌሎች ጉዳዮች ላይም እንደወያኔ ሁሉ የተሳሳተ አቋም መያዛቸው ኃላፊነት የጎደለውና የትግራይን ሕዝብ “እንዲህ ብሎ ያምናል” እያሉ ከሚጠቅሱት ስሕተቱ እንዲታረም እንዲማር ዕድል የማይሰጥ፤ ሕዝብን ለመምራት የተዘጋጀ ፓርቲና ኃይል ሊወስደው ከሚገባው ኃላፊነትና ተጋፍጦ (risk) አንጻር የማይጠበቅ፣ ዘለቄታዊ ለሆነ የሀገር ጥቅም የማይበጅ በመሆኑ የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ወይም አቋም ነው የሚባሉ ነገሮች በርግጥም የትግራይ ሕዝብ እንደነዚህ ዓይነቶችን ከአንድ ሕዝብ የማይጠበቁና አሳፋሪም የሆኑ አቋሞችን ይዞ ከሆነ ሕዝቡ የያዘው አቋም ትክክል እንዳልሆነ እየተናገሩ ከወዲሁ ካልተጋፈጡትና አቋም ካልያዙበት በስተቀር ወያኔ ከወደቀ በኋላም “አሁን ለጊዜው ከትግራ ሕዝብ ጋር ላለመቀያየም ድጋፉን ላለማጣት” በሚል ትክክል እንዳለመሆኑ የያዙትን አቋም ሊለውጡ የሚችሉበትን ዕድል እንደማያገኙ እያወቁ አቋም ለመውሰድ ባለመፈለጋቸው፡፡

ምክንያቱም እነኝህ ወገኖች ማለትም ደሚሕትና አረና ትግራይም ሥልጣን ይዘው ሕዝብን ለማሥተዳደር እንደመፈለጋቸው ወደፊት የሚፈልጉትን ሥልጣን ሊያገኙት የሚችሉት በሕዝብ ምርጫ በመሆኑ ትክክልና መፈጸም ያለበትን ጉዳይ ሁሉ “የትግራይ ሕዝብ ይህ እንዲሆን ስለማይፈልግ” እያሉ “ድጋፉን ላለማጣት በዚህ ወቅት አቋም ልንይዝበት አንችልም ከድል በኋላ ግን አይቸግረንም” ብለው በትግል ወቅት ቀጥሮ ይዘውለት የነበረውን ጉዳይ ከድል በኋላ አሁን ጊዜው ነውና ለሕዝቡ እናውጅ ቢሉ በሕዝብ ተመርጠው ሥልጣን ይዘው ለማሥተዳደር ያላቸውን ምኞት ይሄንን ትክክለኛ እርምጃ በመውሰዳቸው ምክንያት ሕዝቡ ስለሚከፋባቸው በዚህ ምክንያት በሕዝቡ ተመርጠው ሥልጣን መያዝ የሚችሉበትን ዕድል ሊያገኙ ስለማይችሉ ሥልጣኑን ደግሞ ማጣት ስለማይፈልጉ ያኔም ቢሆን “የትግራይን ሕዝብ ያስከፋብናል” በሚል ምክንያት አቋምና ውሳኔ የመውሰድ አቅሙን ቁርጠኝነቱን ዕድሉን ሊያገኙ ከቶውንም ስለማይችሉና መወሰን አቋም መያዝና ሕዝቡንም ማረም ማስተማር ማሳመን ካለባቸው ትክክለኛው ሰዓት አሁን ሆኖ እያለ ይሄንን ማድረግ ባለመፈለጋቸው ነው፡፡

አሁን የሸአቢያ ምኞትና ዝግጅት ደሚሕትን (ትሕዴንን) አጠናክሮ ከእነሱ ጋር በመሆን ወያኔን ጥሎ በኢትዮጵያ ላይ የእሱ ታዛዥ ጥቅም አስከባሪ የሆነ የትሕዴንን መንግሥት መሥርቶ ኢትዮጵያን እየቦጠቦጠ የአፍሪካ ሲንጋፖር ሲል የሚጠራትን ኤርትራን መገንባት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ያለህ አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው “የግድህን ከእንቅልፍህ መንቃት! ቆራጥ መሆን!” በሸአቢያ ላይ ጥገኛ የሆነ አስተሳሰብ ይዘህ ከነበረ እሱን ጣል እርግፍ አድርግና ዛሬ ነገ ሳትል በእጅህ ባለው ነገር ምን አድርገህ እራስህን

ነጻ ልታወጣ እንደምትችል በአስቸኳይ ጊዜ ሳትፈጅ ምድር አንቀጥቃጭ ዐመፅ ቀስቅሰህ ወያኔን ጠራርገው፡፡ ትንሽ ነው የሚበቃው ይሄንንም ያህል ከባድ አድርገህ አታስበው፡፡ መስሎህ ነው እንጅ እኮ ቆርጠህ የተነሣህ ጊዜማ እኮ ሠራዊቱም ካንተ ጋር ነው የሚሰለፈው፡፡ ሌላ ምንም አማራጭ የለህም ቶሎ ንቃ! ቁረጥ! ጨክን! እርምጃህን ውሰድ፡፡

ለኢሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ሳላሳስብ ማለፍ የማልፈልገው ጉዳይ ቢኖር ሌሎች ጣቢያው ሊገነዘባቸው የሚገባው ጉዳዮችን ሌላ ጊዜ የምመለስበት ሆኖ ለአሁኑ ግን ከላይ ከገለጽኩት ተጨባጭ ሥጋቶችና ከሚታወቁ ብዙ ችግሮች አንጻር በቅርቡ ጣቢያው ለትሕዴን የሰጠውን የአየር ሰዓት ሽፋን ዕድል የኢትዮጵያንና የሕዝቧን ዕድል የሚያስጠብቅ ባለመሆኑና ኢሳት እንደ የሕዝብ ልሳንነቱ ለሀገርና ለሕዝብ ካለው ዓላማና ሕልም አንጻር ይህ የወሰደው ውሳኔ ተጻራሪ በመሆኑ ይሄንን የተሳሳተ ውሳኔውን በፍጥነት እንዲያጥፍ እንደ አንድ ዜጋ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ አዝማሚያቹህ እንደሚጠቁመው ለሌሎች ኃይሎችም ተመሳሳይ ዕድል የመስጠት ዝንባሌ ያላቹህ መስሎ ስለተሰማኝ በተለይ የኦነግ ኃይልም ተመሳሳይ ጥያቄ ቢያቀርብ እንደምታውቁት ሁሉ ይህ ኃይል ኢትዮጵያ ውስጥ ከወያኔ ጋር በመተባበር የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸመና ወደፊትም ለመፈጸም ሕዝብን የሚመርዙ የጥፋት ስብከቶቹን እንደ ጁሀር ያሉ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን በመጠቀም እየነዛ ያለ የጥፋት ኃይል በመሆኑ ዕድሉ እንዳይሰጠው ይልቁንም ያንን የዘር ማጥፋት ወንጀል ትዕዛዝ ሰጥተው ያስፈጸሙ አመራሮቹንና ታጣቂዎቹን ከያሉበት ለፍርድ ሊቀርቡ በሚችሉበት ጉዳይ ላይ የሚጠበቅባቹህን እንድታደርጉ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ወያኔም ወያኔ ፤ ሽአቢያም ሽአቢያ

አምላክ ያመጣብን ፤ መቅጫ ማስተማሪያ

ግን እኛም አልተማርን ፤ በዚህ በታረሚያ

ጌታ እንዴት ታደርገን ፤ እኛን እዚህና እዚያ

ቀኑስ እንዴት ይሆን ፤ ነገ ከነገ ወዲያ

እጣዋስ ምንድን ነው? ፤ ይህች ሀገር ኢትዮጵያ

ከጅቦች አፍ ገብታ ፤ ሳትደቅ እንደ ሥጋ

የምትተርፍበትን ፤ ታምርህን ስጓጓ

ከበቀደም ትናንት ፤ ከትናንትም ዛሬ

እንዲህ አወሳስበህ ፤ የሰጠኸን ለአውሬ

በቃ ላትል ነው ወይ? ፤ ልንቀር በመረሬ፡፡

በደል ብንበድልህ ፤ ብናምፅም በአንተ

እስከ አሁን ያየነው ፤ በሁሉ የተጋተ

እሱ በቂ ሆኖ ፤ ሒሳቡ ሊዘጋ

በቃቹህ ልትለን ፤ መስሎኝ ቀን ሊነጋ

ለካ እሱ ገና ነው ፤ የዐመፃችን ዋጋ

ከትናንትም ዛሬ ፤ ከዛሬም ለነገ

መቷል መዓት መከራ ፤ መርግ የተመረገ

የዚህ ዘመኑ ሕዝብ ፤ ካለህ ቅን ልቡና

ይሄ ሁሉ ቅጣት ፤ የግፍ ግፍ ገመና

ውርደት ውድቀት ጉዱ ፤ የማያልቅ ቀኖና

ይደፍረኛል ብለህ ፤ ባልገመትከው መና

ስትንቀው በኖርከው ፤ ያበላህ ያሳር ቁና

የናቁት ያደርጋል ፤ ያስቀራል እራቁት

ተብሎ የተተረተው ፤ ደርሶብህ እንደትንቢት

በሠራኸው ኃጢአት ፤ በዐመፃህ ነውና

መከራ ላይ ችጋር ፤ በያይነት ፈተና

እየደራረበ ፤ ያሸከመህ ጫና

መክሮህ አስተምሮህ ፤ ለዚያ ሕይዎት አብቂ

ለአምላክ ያደረ ፤ ቃል ሕጉን ጠባቂ

አባት ሐዋርያ ፤ ባይኖርም አጽዳቂ

በአምላክ ላይ ዐምፆ ፤ ከእጁ ማምለጥ ደኅና

ከቶ የማይታሰብ ፤ የማይሆን ነውና

ባንዣበበው እሳት ፤ ተበልተን ሳንጠፋ

ይሄን ጊዜ ፈጥነን ፤ ንስሐ እንግባ

በልቶ ሳይጨርሰን ፤ ጭራቅ እያደባ፡፡

መሐሪው ፈጣሪ ፤ ፈልጎ ሊምረን

አጥብቆ ሲጠራን አጥብቀን ከሸሸን

መግቢያችን ገደል ነው ፤ እየተጠላለፍን፡፡

ንስሐችን ገብተን ፤ በጽድቁ ብናድር

በዐመፃችን ምክንያት ፤ ሆኖ ታላቅ ቀንበር

እንደ ጋራ ከብዶ ፤ የተጫነን ጠጠር

ከጠጠርም ቀሎን ፤ ባገኘነው ነበር፡፡

ንስሐ ካልገባን ፤ በፀመፃ ከቀጠልን

ጠጠሩ እንደጋራ ፤ ከብዶ እንደተጫነን

እሾኩ የጦር ያህል ፤ ሰቅዞ እንደወጋን

እንኖራለን እንጅ ፤ ግፍ እየተጋትን

ግፈኞች ተነቅለው ፤ አይመጣም መልካም ቀን፡፡

ንስሐ እንግባ ፤ እንበለው ማረን

ምህረቱን እንዲያወርድ ፤ ከአሳር እንዲያወጣን

እሾኩን እንደሾከ ፤ ጠጠሩን እንደጠጠር

ነቅለን አስፈንጥረን ፤ ሰላም እንድንኖር

ይሄንን ለማድረግ ፤ እንዲያስችለን እግዜር፡፡

እሽ በጅ ብትሉ ፤ ለኔ ብትታዘዙ

የምድርን በረከት ፤ ትበላላቹሀ ብዙ

እንቢ ብትሉ ግን ፤ በእኔም ብታምፁ

ሰይፍ ይበላቹሀል ፤ እንድትገሰፁ

ብሏልና ቃሉ ፤ ይሄው ነው ሕግ ደንቡ

ምህረቱን ካሻቹሀ ፤ ንስሐውን ግቡ፡፡

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!